# በሲያትል የሰሜን-ምዕራብ አሜሪካ የቅንጅት ቻፕተር
# SEATTLE NORTHWEST KINIJIT CHAPTER

=====================================================================

ታሕሳስ 22 ቀን 2000 ዓ. ም.

**ቅንጅት ለቆመላቸው ሕዝባዊ አላማዎች መሳካት ድጋፋችን ተጠናክሮ ይቀጥላል ለአምባገነንነት ግን ቦታ የለንም።**

እኛ በሲያትልና አካባቢው የምንገኝ የቅንጅት ደጋፊ ኢትዮጵያውያን ምንጊዜም ቢሆን ለምንወዳት ሃገራችንና ሕዝባችን በጎውን ሁሉ እንመኛለን። ትግላችንን አጠናክረን ለመቀጠል እ.ኤ.አ. December 16, 2007 ታላቅ ሕዝባዊ ስብሰባ ተጠርቶ 12 የስራ አስፈጻሚ አባላት በሕዝብ ተመርጠው ስራቸውን ቀጥለዋል። ዘላቂ የዳበረና ሕዝባዊ መሰረት ያለው ዴሞክራሲያዊ ስርዓት በኢትዮጵያችን ለማምጣት የቅንጅት ፓርቲ የሚያደርገውን ሁለንተናዊ ትግል አያደነቅን፤ ከኛ የሚጠበቀውን ድጋፍ ሁሉ በበለጠ አጠናክረን እንቀጥላለን። በአንፃሩም በቅንጅት ፓርቲ ውስጥ የህግ የበላይነት ተጠያቂነትና የዲሞክራሲ እሴቶች በተግባር ላይ መዋል ለትግሉ መሳካት መሰረቶች ናቸው ብለን እናምናለን። ከዚህ የተለየ አካሄድ የቅንጅት መንገድ አይደለም።

በሚያሳዝን መልኩ አደባባይ የወጣውን አወዛጋቢውን የቅንጅት ሊቀመንበር ኢንጅነር ሃይሉ ሻውልን እንቅስቃሴ በትእግስትና በአንክሮ ስንከታተል ቆይተናል። ሁኔታዎች ከመሻሻል ይልቅ ሕዝብን ይበልጥ እያሳዘኑና ትግሉን እየጎዱ ይገኛሉ። እርግጥ ነው ሊቀመንበሩ ላደረጉት በጎ የትግል አስተዋፅዖ ሊመሰገኑ ይገባል። ይሁንና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የሚያደርጓቸው እንቅስቃሴዎች የቅንጅትን መርህና መተዳደሪያ ደንብ ያልተከተሉና ትግሉን የሚያዳክሙ ሆነዋል። ከነዚህም ውስጥ፦

1. መፍረሱን በፊርማቸው ያፀደቁትን አወዛጋቢውን "የቅንጅት አለም አቀፍ ካውንስል"ን ጉዳይ በተመለከተ፦ የፓርቲውን ትእዛዝና አቋም በመፃረር በግላቸው የዚሁን አካል መኖር በተደጋጋሚ ማወጃቸው
2. ፓርቲው ከሰጣቸው ስልጣን ውጭ አምስት ታላላቅ የቅንጅት መሪዎችን ከአመራር አግጃለሁ ብለው መግለጫ ማውጣታቸው
3. የቅንጅት ላዕላይ ምክር ቤትም ሆነ ስራ አስፈፃሚው አካል በጽህፈት ቤቱ ውስጥ እንዳይሰበሰብ ለፓርቲው ሳይሆን ለራሳቸው ለኢንጅነር ሃይሉ ታዛዥ በሆኑ በፈረሰው በቀድሞው መ.ኢ.አ.ድ. ስም በሚንቀሳቀሱ ጥቂት ሰዎች አማካኝነት በተደጋጋሚ ማስከልከላቸው
4. ይባስ ብሎም የግል ድርጅት በሚያስመስል መልኩ የፓርቲውን መተዳደሪያ ደንብ በተፃረረ መልኩ ተጠባባቂ ሊቀመንበር ሾሜያለሁ ማለታቸውና ተመሳሳይ አምባገነናዊ አካሄዶች እጅጉን አሳዝነውናል።

Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

ጨቋኙ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ የሚያደርሰው ወከባና እንግልት አልበቃ ብሎ በሊቀመንበሩና ከሳቸው ጋር ባበሩ ቡድኖች በቅንጅት ፓርቲና አመራሩ ላይ የሚደርስበት እንቅፋት ያበሳጨን ጉዳይ ነው ባስችኳይም መፍትሄ ይስፈልገዋል ብለን እናምናለን።

እነዚህንና የተያያዙ አንገብጋቢ ጉዳዮችን አልባት ለመስጠት የቅንጅት ላዕላይ ምክር ቤት ታሕሳስ 20 ቀን 2000 ዓ. ም. በአዲስ አበባ ባደረገው ጠቅላላ ጉባኤ የወሰናቸውን ደንብን የተመረኮዙ ውሳኔዎች እያደነቅን በፍጥነት ተግባራዊ እንዲደረጉ አያይዝን እናሳስባለን። በውሳኔዎቹ መሰረት የተጓደሉ የላዕላይ ምክርቤት አባላት ተተክተው፤ ስራአስፈፃሚው አካልም የተሰጠዉን ሙሉ መብት ተጠቅሞ አንገብጋቢ የሆኑ የፓርቲው ቁልፍ ጉዳዮች ላይ የተፈጠኑ ውሳሌዎች እንዲሰጥ የበኩላችንን በድጋሚ እናሳስባለን። ድጋፋችን ከቅንጅት መርሆዎች የመነጨ ነው። በኢትዮጵያችን ለሚደረገው ሕጋዊና ሰላማዊ ትግል ተስፋ ለሆነው የቅንጅት ፓርቲ የላዕላይ ምክር ቤትና ስራ አስፈፃሚ ውሳኔዎች ያለንን ድጋፍ አጠናክረን እንቀጥላለን።

ቅንጅት ለሰላም፣ ለፍትሕ፣ ለአንድነት፣ ለዲሞክራሲና ለብልፅግና!!!

**በሲያትል የሰሜን-ምዕራብ አሜሪካ የቅንጅት ቻፕተር ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ**

ሲያትል-ዋሽንግተን።

Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com